City of Seattle

Democracy Voucher Program
P.O. Box 94729
Seattle, Washington 98124-4729

PRSRT STD
U.S. POSTAGE
PAID
SEATTLE WA
PERMIT 2052

100 ዶላር ዋጋ ያለውን የዴሞክራሲ ኩፖንዎን ለማግኘት ዛሬውኑ ያመልክቱ!

Amharic



በሲያትል ምርጫ ለመሳተፍ አዲስ አይነት መንገድ አለ!

100 ዶላር ዋጋ ያለውን የዴሞክራሲ ኩፖንዎን ለማግኘት ዛሬውኑ ያመልክቱ!
www.seattle.gov/democracyvoucher

አማርኛ • Khmer • 繁體中文 • 简体中文 • Tagalog • 한국어 • ພາສາລາວ •
Oromiffa • русский язык • af Soomaali • Español • ภาษาไทย • ትግርኛ • Tiếng Việt

የዴሞክራሲ ኩፖኖችን በ2017ቱ የሲያትል ምርጫ ለሲያትል ከተማ ምክር ቤት ወይም ለከተማ አቃቤ-ሕግ የሚወዳደሩ እጩዎችን ለመደገፍ ሊጠቀሟቸው ይችላሉ፡፡

1. ኩፖኖችን ከጃኑዋሪ 3/2017 በኋላ በመልዕክት መቀበያ ሳጥንዎ ይፈልጉ።

2. በድረ ገጻችን ላይ ብቁ የሆኑ እጩዎችን ዝርዝር ይፈልጉ እና ኩፖንዎን ይመድቡ።

3. ኩፖኖችዎን ለእጩው የዘመቻ ቡድን ይስጡ ወይም ለሲያትል ከተማ የሥነ-ምግባር እና ምርጫ ጉዳዮች ኮሚሽን በመልዕክት ሳጥን ይላኩ።

4. እጩው ከኩፖንዎ ላይ ገንዘቡን ያገኛል።

5. በምርጫው ሂደት ሁሉ እጩዎን ይከታተሉ!

እጩዎችን ለማግኘት፡
www.seattle.gov/democracyvoucher

የዴሞክራሲ ኩፖኖቼን እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ከሆነ፣ 100 ዶላር ዋጋ ያላቸውን የዴሞክራሲ ኩፖኖችን ለማግኘት ብቁ ይሆናሉ፡-

- የሲያትል ነዋሪ ከሆኑ፣
- ዕድሜዎ ቢያንስ 18 ዓመት ከሆነ፣ እና
- ወይ፡- የአሜሪካ ዜጋ፣ ወይም በትውልድ አሜሪካዊ አለበለዚያ ደግሞ ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ ("ግሪን ካርድ ባለቤት ከሆኑ")፡፡

የተመዘገቡ መራጮች ከጃኑዋሪ 3/2017 በኋላ በቀጥታ የነጠላ ዋጋቸው 25 ዶላር የሆኑ አራት የዴሞክራሲ ኩፖኖችን ያገኛሉ፡፡

የዴሞክራሲ ኩፖኖችን ለማግኘት ለመራጭነት መመዝገብ አይጠበቅብዎትም ድረ ገጹን በመጎብኘት ዛሬውኑ ያመልክቱ!

www.seattle.gov/democracyvoucher

City of Seattle

በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

የዴሞክራሲ ኩፖኖች ምንድናቸው?

የዴሞክራሲ ኩፖኖች ለሲያትል ከተማ ምክር ቤት ወይም ለከተማ አቃቤ-ሕግ የሚወዳደሩ እጩዎችን ዘመቻ ለመደገፍ እርስዎ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ የወረቀት ካርዶች ናቸው፡፡ ብቁ የሆኑ የሲያትል ከተማ ነዋሪዎች የነጠላ ዋጋቸው 25 ዶላር የሆነ አራት ኩፖኖችን ያገኛሉ፡፡ በአገሪቱ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የታየ እንደመሆኑ፣ የዴሞክራሲ ኩፖን ፕሮግራም ለሲያትል እጩዎች ዘመቻዎች አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ የሲያትል ዜጎችን ቁጥር መጨመርን ዓላማ ያደረገ ነው፡፡

የዴሞክራሲ ኩፖን ፕሮግራም የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኘው እንዴት ነው?

በ2015፣ የሲያትል መራጮች በዜጎች የሚመራውን "ሐቀኛ የሲያትል ምርጫ" ("Honest Elections Seattle" (I-122)) የተሰኘውን እንቅስቃሴ አጸደቁ፡፡ ይህ እንቅስቃሴ ፕሮግራሙን ለቀጣዮቹ 10 ዓመታት በገንዘብ ለመደገፍ በዓመት 3 ሚሊዮን ዶላር ከፍተኛ የንብረት ታክስ እንዲሰበሰብ አጽድቋል፡፡ የዴሞክራሲ ኩፖኖቹ አንድን አማካይ የቤት ባለቤት በዓመት 11.50 ዶላር ያስወጣሉ፡፡

የሲያትል የሥነ-ምግባር እና የምርጫ ጉዳዮች ኮሚሽን ሚና ምንድነው?

የሲያትል የሥነ-ምግባር እና የምርጫ ጉዳዮች ኮሚሽን ወገንተኛ ያልሆነ፣ ገለልተኛ የከተማ ኮሚሽን ሲሆን የሲያትል ከተማን የሥነ-ምግባር፣ የምርጫ፣ የቅስቀሳ እና የጥቆማ ሕጎችን ያስፈጽማል፡፡ በመራጮች በጸደቀው I-122 እንቅስቃሴ መሰረት፣ ኮሚሽኑ የዴሞክራሲ ኩፖን ፕሮግራምን ያስተዳድራል የሒሳብ ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

የዴሞክራሲ ኩፖን ፕሮግራም ዓላማ ምንድነው?

የዴሞክራሲ ኩፖን ፕሮግራም የሲያትል ነዋሪዎች በአካባቢያቸው መንግስት ውስጥ የበለጠ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚያስችል አዲስ መንገድ ነው፡፡ የዴሞክራሲ ኩፖን ፕሮግራም ለአካባቢያዊ ዘመቻዎች አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ የሲያትል ዜጎችን ቁጥር መጨመርን ዓላማ ያደረገ ነው፡፡

የዴሞክራሲ ኩፖኖቼን በምን መልክ ልጠቀም እችላለሁ?

ብቁ ለሆኑ እጩዎች፣ ከዴሞክራሲ ኮፖኖችዎ መካከል አንድ(25 ዶላር)፣ ሁለት(50 ዶላር)⊠ ሦስት(75 ዶላር)፣ ወይም አራቱንም(100 ዶላር) ሊሰጡ ይችላሉ። ኩፖኖች ሊፈረሙና ቀን ሊጻፍባቸው ይገባል፤ እንዲሁም የእጩው ስም በኩፖኑ ላይ በግልጽ በሚታይ መልክ መጻፍ አለበት፡፡ ኩፖኖች በቀጥታ ለእጩው ዘመቻ ቡድን ሊመለሱ ወይም ለሲያትል የሥነ-ምግባር እና የምርጫ ጉዳዮች ኮሚሽን (Seattle Ethics and Elections Commission) ሊመለሱ ይችላሉ፡፡

የዴሞክራሲ ኩፖኖቼን መቼ አገኛለሁ?

ለመራጭነት ተመዝግበዋል? እንግዲያው ከጃኑዋሪ 3/2017 በኋላ በመልዕክት አድራሻዎ በኩል የዴሞክራሲ ኩፖን ይደርስዎታል፡፡

ለመራጭነት አልተመዘገቡም? www.seattle.gov/democracyvoucher የሚለውን ድረ ገጽ በመጎብኘት የዴሞክራሲ ኩፖኖችን ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ፡፡ ማመልከቻዎ ከተጣራ በአጭር ጊዜ ውስጥ የዴሞክራሲ ኩፖኖችዎን ያገኛሉ፡፡

ኩፖኖቼን ልጠቀምባቸው አልፈልግም፡፡ የዴሞክራሲ ኩፖኖቼን አሳልፌ መስጠት እችላለሁ?

የዴሞክራሲ ኩፖኖች የሚመደቡት ለእርስዎ እና ለእርስዎ ብቻ ነው፡፡ ኩፖኖች፣ አይሸጡም፣ በስጦታ አይሰጡም ወይም አይገዙም፡፡ የዴሞክራሲ ኩፖኖች የገንዘብ ዋጋ የላቸውም፣ እና ንብረት አይደሉም፡፡

www.seattle.gov/democracyvoucher **(206) 727-8855** **democracyvoucher@seattle.gov**

AM ከጃንዋሪ 2017 ጀምሮ፣ የሲያትል አዲሱ የዲሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ግብር በአካባቢ ምርጫዎች እርሰዎ እንዲሳተፉ ቀላል አድርጎታል፡፡ የበለጠ ለማወቅ እና ለማመልከት፤ይጎብኙ **www.seattle.gov/democracyvoucher/amharic**

KM ការចាប់ផ្តើមនៅខែមករា ឆ្នាំ 2017 កម្មវិធីប័ណ្ណប្រជាធិបតេយ្យថ្មីរបស់ទីក្រុងស៊ីថល Seattle ដែលធ្វើឱ្យវាមានភាពងាយស្រួលជាងមុនសម្រាប់លោកអ្នក ដើម្បីចូលរួមក្នុងការបោះឆ្នោតនៅមូលដ្ឋាន។ ដើម្បីស្វែងយល់បន្ថែមទៀត និងអនុវត្ត សូមចូលទៅកាន់គេហទំព័រ៖ **www.seattle.gov/democracyvoucher/khmer**

CH 自2017年1月起，西雅图的全新“民主代金券计划”让您能够更轻松地参加地方选举。欲了解更多信息，请访问：**www.seattle.gov/democracyvoucher/chinese-simplified**

CH 自2017年1月起，西雅圖的全新「民主代金券計劃」讓您能夠更輕鬆地參加地方選舉。欲瞭解更多資訊，請造訪：**www.seattle.gov/democracyvoucher/chinese-traditional**

TA Simula Enero 2017, magiging mas madali na para sa inyo ang makilahok sa mga lokal na halalan sa pamamagitan ng bagong Programa ng Seattle na Voucher ng Demokrasya (Democracy Voucher Program). Para sa karagdagang kaalaman at para magpalista, bisitahin ang **www.seattle.gov/democracyvoucher/tagalog**

KO 2017년 1월부터 시애틀의 새 민주주의 바우처 프로그램을 통해 귀하가 지역 선거에 더 쉽게 참가할 수 있게 됩니다. 더 자세히 알아보고 신청하려면 **www.seattle.gov/democracyvoucher/korean**를 방문하십시오.

LA ເລີ່ມແຕ່ເດືອນມັງກອນ 2017 ເປັນຕົ້ນໄປ, ໂຄງການໃໝ່ບໍລິຈາກເພື່ອປະຊາທິປະໄຕຂອງເມືອງຊີອາເຕີ້ລ ເຮັດໃຫ້ທ່ານເຂົ້າຮ່ວມໃນການເລືອກຕັ້ງຂອງທ້ອງຖິ່ນໄດ້ງ່າຍຂຶ້ນ. ເພື່ອຮຽນຮູ້ເພີ່ມເຕີມ ແລະ ນຳໃຊ້, ກະລຸນາເຂົ້າເບິ່ງ **www.seattle.gov/democracyvoucher/lao**

OM Jalqaba baatii Amajjii 2017tti, Sagantaan Nagahee Dimokraasii Siyaatil haarawaan akka filannorratti hirmaataniif isiinii mijesseera. Caalaa hubachuufi iyyachhuf **www.seattle.gov/democracyvoucher/oromo** doowadhaa.

RU Новая программа города Сиэттл «Ваучер демократа» облегчит ваше участие в местных выборах с января 2017 года. Чтобы узнать о программе больше и зарегистрироваться в ней, посетите сайт **www.seattle.gov/democracyvoucher/russian**

SO Bilowga jaanayo 2017, Barnaamijka Foojarka Dimuqraadiga cusub ee Seattle waxay kuu sahlaysaa inaad ka qayb qaadato doorashooyinka deegaanka. Si aad u barato wax badan iyo codisga, booqo **www.seattle.gov/democracyvoucher/somali**

ES A partir de enero de 2017, el nuevo Programa de Vales Democráticos le facilita la tarea de participar en las elecciones locales. Para conocer más y solicitudes, visite **www.seattle.gov/democracyvoucher/spanish**

TH เริ่มตั้งแต่มกราคม 2017 โครงการบัตรกำนัลเพื่อสนับสนุนระบอบประชาธิปไตยซึ่งเป็นโครงการใหม่ของเมืองซีแอตเทิลช่วยให้คุณสามารถเข้าร่วมในการเลือกตั้งท้องถิ่นได้ง่ายขึ้น เรียนรู้เพิ่มเติมและขอรับได้ที่ **www.seattle.gov/democracyvoucher/thai**

TI ካብ ጥሪ 2017 ጀሚሩ፣ ሓዲሽ ናይ ሲያትል ዲሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ኣብ ከባቢያዊ ምርጫታት ብቐሊሉ ክትሳተፍ የኽእለካ። ዝያዳ ሓበሬታ ንምፍላጥን ንምምልካትን፣ **www.seattle.gov/democracyvoucher/tigrigna** ተወከስ።

VI Bắt đầu từ tháng 1 năm 2017, thành phố Seattle cho phép bạn tham gia dễ dàng hơn vào các cuộc bầu cử địa phương qua chương trình Vé Phiếu Dân Chủ (Democracy Voucher). Để biết thêm chi tiết và đăng ký, bạn có thể truy cập qua trang mạng **www.seattle.gov/democracyvoucher/vietnamese**